# <u>የጦርነት ነጋሪትና የአካባቢው ሁኔታ</u>

በአፍሪካ ቀንድ ማለትም ኢትዮጵያ በምትገኝበት አካባቢ ያለው የጦርነትና ግጭት ሁኔታ እየተባበሰ የሚሄድ ነው በሚል ውስጠ አዋቂዎች ያሳስባሉ፡፡ የአካባቢውን ሁኔታ በሚመለከት እስቲ በዝርዝር እንቃኘው፤

የወያኔ አገዛዝ ኤርትራ ላይ ጦርነት ለመክፈት እየተዘጋጀ ነው የሚሉ መረጃዎች አሉ፡፡ ወደ አሰብ ግንባር ሁለቱም ተፃራሪዎች ወታደርና መሳሪያ እያጓጓዙ ናቸው፡፡ የወያኔ አገዛዝ የኤርትራ ተቃዋሚዎችን በየፈርጁ ለማቀነጃጀት ደፋ ቀና እያለም መሆኑ ታውቋል፡፡ በቅድሚያ አፋሮችና ኩናማዎችን አጣምሮ ከነዚሁም ጋር የሳሆ/አሳውርታ ድርጅትንና የአናሳ ብሄረሰቦችን ስብስቦች ለማቀናጀት ተነስቷል፡፡ ወደ ሐምሌ መጨረሻ ላይም የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች " ብሔራ ዊ ጉባዔ" በአዲስ አባባ ይካሄዳል ተብሏል፡፡ የወያኔ አገዛዝ ቶሎ ቶሎ ተሰባሰቡ ተቀናጁ ግፊት ምናልባትም ለታቀደ ወረራ ቀዳሚ ዝግጅት ሊሆን ይችላል የሚሉ አሉ፡፡ መለስ የትግራይ ጄኔራሎችን ብቻ እየሰበሰበ ያማክራል የሚልም መረጃ ቀርቧል፡፡ መለስ ዜናዊ ከዚህ ቀደም በተደረገው ጦርነት ከጦሩም ከሕዝብም በኩል ያገኘውን ድጋፍ በዛሬው ጊዜ አገኛለሁ ብሎ ካሰበ ተሳስቷል የሚሉ ክፍሎች በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስን ጦርነት የሚያጅብበት ሁኔታ ከቶም አይከሰትም ይላሉ፡፡ ጦሩም ቢሆን የቀድሞ አንፃራዊ ውህደት ያለው ሳይሆን ይበልጥ የተከፋፈለና የተዳከመ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ ወያኔ የኤርትራው ገዢ ድርጅት ተጠልቷልና ወረራው ይቀላል ብሎ የሚያስበውም ከኤርትራ ፀረ ወያኔ ብሄራዊ ስሜት ጋር የሚጋጭ ነው የሚሉ ክፍሎች ጦርነቱ ከተነሳ ለራሱ ለወያኔም መለብለቢያ እሳት ሊሆንበት ይችላል ሲሉ ያሳስባሉ፡፡ በቅርቡ ሻዕቢያ ከጅቡቲ ጋር ያለውን ችግር ለመፍታት መቻሉና የቃታር ወታደሮች ቁጥራቸው ባይበዛም በጅቡቲና ሻዕቢያ መሀል መስፈራቸው ለወያኔ ድንገተኛ ዜና ሆኖ እንዳስ ደነገጠውና በጅቡቲው ፕሬዚዳንት አማር ገሌ ላይም ቅሬታ እንዲይዝ እንዳደረገው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሻዕቢያና ጅቡቲ ከተስማሙ ከሻዕቢያ እርዳታ ማግኘት ጀምረው የነበሩት የጅቡቲ አማፅያን ማለትም የፍሩድ እንቅስቃሴ ችግር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የወያኔ አገዛዝ ከምዕራባውያን ጋር በመመሳጠር የደቡብ ሱዳንን መገንጠል ለመደገፍ መሰማራቱ በመረጃ እየተረጋጋጠ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የነገይቷ ነፃ ደቡብ ሱዳን የፖሊስ ና የጦር አዛዦች የሚሆኑ ወደ መቀሌ መጥተው ስልጠና እየተሰጣቸው መሆኑን ኢሕአፓ አጋልጧል፡፡አሜሪካ ለደቡብ ሱዳን እውቅናና እርዳታ እንደምትሰጥ ገልጣለች፡፡ የደቡብ ሱዳን አማፅያን መሪ በአውሮፕላን አደጋ ሞተ የተባለውም ዛሬ አጠያያቂ እየሆነ መምጣቱም መጠቀስ ያለበት ነው፡፡ ሚቹ መሪ ጆን ጋራንግ አዲሲቷ ሱዳንን እንመሰርታለን ባይ እንጂ መገንጠልን አጥብቆ የሚቃወም ስለነበር አደጋ የተባለው አደጋ ሳይሆን የተዘጋጀ ግድያ ነው የሚሉ ዛሬ በዝተዋል፡፡ ምዕራባውያን ደቡብ ሱዳንን ለማስገንጠል ሲጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ ግብፅና ሌሎች የአረብ ሀገሮች ደግሞ ይህን ለማደናቀፍ እያሴሩ መሆናቸው የሚታወቅ ነው፡፡ የሱዳኑ በሺር

ቢሆንም በደቡብ ሱዳን ያለውን የአካባቢ መንግስት የሚቃወሙ ሚሊሺያዎችንና ፀረ ዲንካ አናሳ ጎሳዎችን አስታጥቆ ማሰማራቱ ይነገራል። እነዚህ ሚሊሺያዎች ባለፈው ዓመት እስከ 3 ሺ ሰው ገድለዋል ተብሎም ተጋልጧል።ደቡብ ሱዳን ብዙ ጎሳዎችን ያቀፈች ስትሆን የዲንካ ጎሳ የፖለቲካ ስልጣኑን በእጁ ይዟል ብለው የሚቃወሙ ጥቂቶች አይደሉም። ስለዚህም በመጪው ዓመት የታቀደው ውሳኔ ሕዝብ በሰላም መካሄዱ አጠራጣሪ መሆኑ ይተነበያል። በሰላም ተካሂዶ ቢገኝና ደቡብ ሱዳን ብትገነጠል ይህ የመገንጠል ወረርሽኝ ወደ ዳርፉርም መዛመቱ የሚጠበቅ መሆኑን ታዛቢዎች ያረጋግጣሉ። በአጭሩ ሱዳን በጦርነት ስትታመስ አካባቢውም ይበልጥ ይረበሻል ማለት ነው። የደቡብ ሱዳን መሪዎች በአብላጫው የኃያሉ መንግስት ቡችሎች በመሆናቸውም ደቡብ ሱዳን ነፃ ብትሆን ነፃ መንግስት የምትመሰርት ሳይሆን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሰለባ መሆኗ ከወዲሁ የሚታወቅ ነው ተብሏል። የዚህም አዲስ መንግስት ሰልፍ ከኢትዮጵያና ከአካባቢው ነፃነት ፈላጊ ሕዝቦች ጋር ሳይሆን ከነወያኔና ምዕራባውያን ጋር መሆኑ መታወቅ ያለበት ነው ሲሉ ታዛቢዎችም ያስጠነቅቃሉ።

ወደ ሶማሊያ ስንመለከትም አክራሪ ቡድኖች እርሰ በርስ ቢፋለሙም ሽግግር መንግስት ተብዬው በእግሩ መቆም እንዳቃተው በሚካሄደው ጦርነት እየተረጋጋጠ ነው። በሻዕቢያ የሚደገፈው የሼክ አዌይስ ጦርና የአልሻባብ አክራሪዎች አርስ በርስ መዋጋታቸውና መጋጨታቸው ቀጥሏል። የሼክ አህመድ መንግስት ተብዬ ተቋም ደግሞ በሞቃዲሾ እንኳን በበቂ መንቀሳቀስና ቁጥጥሩን ማስፋፋት አልቻለም። በአጭሩ ሶማሊያ በጦርነት እየታመሰች ቀጣይ ናት ማለት ይቻላል። በአንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት ላይ ያለችው ተገንጣይዋ ሶማሊላንድም ብትሆን ውሎ አድር እውቅናና ድጋፍ ስታጣ ወደ ሶማሊያ ማጥ መግባቷ አይቀርም የሚሉ በርክተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ግብፅ የአባይን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ በጦር ልትዘምት ማስፈራራቷን ቀጥላላች። ግብፅ ኢትዮጵያን ትወራለች የሚለው ግምት መሰረተ ቢስ ቢሆንምግብፅ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለመበጥበጥና ለመጉዳት ግን የለመደባትን ጥረቶችና ሻጥሮች ማድረጓ መጠበቅ ያለበት ነው ሲሉ አዋቂዎች ይናገራሉ። በሻዕቢያ በኩል ደግሞ ፀረ ወያኔ ሀይሎችን በማጠናከሩ ረገድ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ደካማና አነጋጋሪ መሆኑም እያደር እየታየ ያለ ነው። የፀረ ወያኔ ሀይሎች መተባበርን በተመለከተ የሻዕቢያ ሚና አዎንታዊ ነው ማለት አይቻለም የሚሉት ክፍሎች ሻዕቢያ ኢትዮጵያ የሚሉ ሀይሎች መጠናከራቸውን ከልብ አይፈልግም ሲሉ ይደመድማሉ። የኢትዮጵያ ሀይሎች መተባባር ሆነ መታገል ግን በሻዕቢያ እጅ ያለ ጉዳይ ባለመሆኑ ድክመቱ ኢትዮጵያውያኑን ራሳቸውን የሚመለከት መሆኑ ሊካድ የሚችል አይደለም ባዮችም ብዙ ናቸው። በዚህም በዚያም ግን የወያኔ አገዛዝ የሕዝብን ትኩረት ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመሳብ ጦርነት ሊጭር ማቀዱ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው። በአካባቢውም የሚከተለው ፖለቲካ የባዕዳንን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንጂ የሀገርና ሕዝብን ጥቅም የሚያስቀድም አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባዕዳን አደብ እንዲገዙና ወያኔን መደገፍ እንዲያቆሙ ሊያደርግ የሚችለውም ባዕዳኑን ራሳቸውን በሚቆነጥጥ ደረጃ ሲንቀሳቀስና እርምጃዎችን ሲወስድም ነው ተብሏል። የቀወሱን ሁኔታ ለመሰረታዊ ለውጥ ልንጠቀምበት የምንችለው ትግላችንን በማፋፋም ብቻ ነው።